መ/ቁ 295430

ቀን 26/12/2014

ዳኞች፡- ነጋሽ ኪዳኔ

ሳሙኤል ታደሰ

ሽፈራው አበበ

ይግባኝ ባይ፡- የወላይታ ህዝብ ዲሞክረሲያዊ ግንባር (ዎህዲግ) ሊቀመንበር አቶ ተክሌ በርና ቀረቡ

መ/ሰጪን፡- የኢት/ያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ነ/ፈጅ አቶ ወንጌል አባተ ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

## ፍ ር ድ

ለዚህ ፍርድ መነሻ የሆነው ይግባኝ ባይ ነሐሴ 04 ቀን 2014 ዓ/ም አሻሽሎ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ሲሆን የቅሬታው ይዘትም በሚከተለው መልኩ ቀርቧል።

በዚሁም መሰረት የኢት/ያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በ01/09/2014 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ ይግባኝ ባይ ማህበር እስከ ሰኔ 10 ቀን 2014 ዓ/ም ባለው የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በፓርቲው ሊቀመንበር በጠቅላላ ጉባኤ እንዲጣራ እንዲሁም ጉባኤ ለማካሄድ የሚያብቃውን ዕቅድ አዘጋጅቶ እስከ ግንቦት 10 ቀን 2014 ዓ/ም ድረስ ለመ/ሰጪ መ/ቤት እንዲገልጽ ያስታወቀው መሆኑን

- በዚሁ መሰረትም ይግባኝ ባይ ማህበር በ03/09/2014 ዓ/ም ዕቅዱን አዘጋጅቶ ለመ/ሰጪ መ/ቤት የላከ ከመሆኑም በተጨማሪ ይግባኝ ባይ ሰኔ 04 ቀን 2014 ዓ/ም ጉባኤው እንደሚያካሄድና መ/ሰጪም ይህንኑ አውቆ ተወካይ እንዲልክ ግንቦት 13 ቀን 2014 ዓ/ም በፃፈው ደብዳቤ ለመ/ሰጪ መ/ቤት ማስታወቁን

- በመቀጠልም በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሻሻል የሚገባቸው ነጥቦች በማዘጋጀት 30 ገፅ ረቂቅ ሰነድ ግንቦት 25 ቀን 2014 ዓ/ም ለመ/ሰጪ መ/ቤት የላከ መሆኑን
- ይግባኝ ባይ ግንቦት 03 ቀን 2014 ዓ/ም ለመ/ሰጪ በቀረበው ዕቅድ መሰረት ይግባኝ ባይ ከገባኤ አደራጅ ኮሚቴ ጋር በመሆን መቀጠሉን
- ይግባኝ ባይ ማህበርሰ ሰኔ 04 ቀን 2014 ዓ/ም ለሚያካሄደው ጉባኤው እንዳይካሄድ በመከልከል ለምን እንደተከለከለ የሚገልጽ በ01/10/2014 ዓ/ም የተጻፈ ደብዳቤ ይግባኝ ባይ ማህበር ከመ/ሰጪ መ/ቤት እንዲወስድ የተገለፀለት መሆኑን
- ይግባኝ ባይ በመ/ሰጪ ሰኔ 01 ቀን 2014 ዓ/ም የተፃለት ደብዳቤ በ03/10/2014 ዓ/ም ከመ/ሰጪ መ/ቤት የወሰደው ሲሆን የጉባኤው አደራጅ ኮሚቴ በምን መስፈርት እንደረደራጀ እስከ አሁን ምን እንደሰራ የሚገልጽ ቃለ ጉባኤ ካልቀረበ በስበስተቀር ይግባኝ ባይ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤውን እንዲያካሄድ የሚከለክል መሆኑን ማረጋገጡን
- ይህ በእንዲህ እያለ ግን የይግባኝ ባይ ኦዲትና ኢንስፔክሽ ኮሚቴ ግንቦት 15 ቀን 2014 ዓ/ም ለመ/ሰጪ መ/ቤት በጻፈው ደብዳቤ ሊቀመንበሩ ዕቅድ በአግባቡ ያለዘጋጀ ስለሆነ ጠቅላላ ጉባኤው በፓርቲው ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚሽን ነው ሊጣራ የሚገባው በማለት ያስታወቀ መሆኑን
- ይግባኝ ባይ ማህበርም የጉባኤ አደራጅ ኮሚቴ እንዴት እንደተመረጠ ከተመረጠም በኋላ የሰራቸው ስራዎች በመዘርዘር ሁለት ቃለ ጉባኤዎችን ሰኔ 06 ቀን 2014 ለመ/ሰጪ መ/ቤት ያስታወቀ ከመሆኑም በላይ የተቋረጠው የሰኔ 04 ቀን 2014 ዓ/ም የጠቅላላ ጉባኤ ሰብስቤ በሌላ ጊዜ አጀንዳ እንዲያዝ እንዲፈቀድላቸው የመ/ሰጪ መ/ቤት የጠየቀ መሆኑን
- ሆኖም የመ/ሰጪ መ/ቤት ይግባኝ ባይ ማህበር በየጊዜው የጠየቃቸውን ጥያቄዎች መልስ ሳይሰጥ ቆይቶ ሀምሌ 13 ቀን 2014 ዓ/ም የይግባኝ ባይ ማህበር ኢዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤው እንዲጣራ የይግባኝ ባይ ማህበር ሊቀመንበር ያቋቋመው የጠቅላላ ጉባኤ አደራጅ ኮሚቴም በኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ውስጥ ገብቶ እንዲሰራ ለይግባኝ ባይ ማህበር ያስታወቀው እንዲሰራ ለይግባኝ ባይ ማህበር ያስታወቀው መሆኑን
- ሆኖም በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 17(ሐ) (መ) (ሠ) መሰረት ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ጠቅላላ ጉባኤ የመጥራት ስልጣን የሌለው ቢሆንም ስልጣን አለው ቢባል እንኳን ፓርቲው አደጋ አጋጥሞት ሊቀመንበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጠራ

ተገልያለት ፈቃደኛ ሳይሆን በሚቀርበት ጊዜ ሲሆን ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ለሊቀመንበሩ የደረሰው ማሳሰቢያ የለም ስለሆነም ስልጣን በሌለው በፓርቲው ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ የተጠራው ጠቅላላ ጉባኤ ከማህበሩ ህጉ ደንብ ውጭ ስለሆነ ቀሪ ሆኖ ጠቅላላ ጉባኤው መጠራት ያለበት በሊቀመንበሩ ነው እንዲባልልን የሚል ሆኖ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ጥር 01 ቀን 2013 ዓ/ም በሊቀመንበሩ ጠጣርቶ ተካሄደ እንደነበር በዚሁ ጉባኤው ከቀረቡት ኤጀንሲዎች ውስጥ አንዱ የአመራር ምርጫ ማካሄድ ስለነበረ ምርጫው ተካሂዶ ነገር ግን ምርጫው የተጭበረበረ ነው የሚል ቅሬታ ቀረበበት ይህ ቅሬታም ለምርጫ ቦርድ ቀርቦ ውድቅ ተደርገዋል ሆኖም ቅሬታው ውድቅ ለመደረጉ ምክንያት በማህበሩ አባላት መካከል ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አለ መግባባት የተፈጠረ መሆኑን

- ስለሆነም በመ/ሰጪ መ/ቤት በቁጥር አ1162/11/678 በ13/11/2014 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻርልንና የፓርቲው ጠቅላላ ጉባኤ በፓርቲው ሊቀመንበር እንዲራ በኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ በሀምሌ 23 ቀን 2014 ዓ/ም የተጣራው ጉባኤ ውድቅ እንዲደረግ በዚሁ ጉባኤ የተደረገ የአመራር አባላት ምርጫም ሆነ የተሰጡ ውሳኔዎች እንዲሰረዙ ውሳኔ ይሰጥልኝ በማለት ይግባኝ ባይ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

መ/ሰጪም የይግባኝ ባይ የተሻሻለ ቅሬታ ደርሶት ነሐሴ 16 ቀን 2014 ዓ/ም በተፃፈ መልሱ የሰጠበት ሲሆን ይዘቱም በአጭሩ በሚከተለው መልኩ ቀርቧል፡፡

በዚሁም መሰረት የመ/ሰጪ ተቋም ዋነኛ ተግባሩ የፖሎቲካ ፓርቲዎች ስራቸውን በህግ መሰረት መሰረታቸውንና አለመስራታቸውን መቆጣጠር ሲሆን በተለይ በማህበሩ አባላት መካከል አለመግባባት ለሚፈጠርበት ጊዜ ለመ/ሰጪ የሚመጡለትን ቅሬታዎች ተመስርቶ የሚወስዳቸው እርምጃዎች አሉት

መ/ሰጪ ከፖሎቲካ ፓርቲዎች የሚመጡለትን የመተዳደሪያ ደንቦች አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ ይመዘገብላቸዋል፡፡

በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ሊቀመንበሩ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የሚጠራው ከፓርቲው በስራ አስፈፃሚ ጋር በመሆን ሲሆን የጉባኤ አደራጅ ኮሜቴው የሚቋቋመው ምልአተ ጉባኤ አሟልቶ ሲገኝ ብቻ ነው ይህ ቢሆንም ግን ይግባኝ ባይ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ለማካሄድ የግድ 6 ስራ አስፈፃሚ ሊገኝ ሲገባው በተያዘው ጉዳይ ግን የቀረቡት የስራ አስፈፃሚ አባላት ቁጥር

ከመስፈርቱ ወረዳ አራት ብቻ ናቸው የተገኙት ስለሆነም ሊቀመንበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት ስለማይችል ጠቅላላ ጉባኤው በማህበሩ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ እንዲጣራ ተደርገዋል፡፡

- በስር አስፈፃሚው ኮሚቴ መካከል አለመግባባት ስለተፈጠረ ነው ምልአተ ጉባኤው ሳይሟላ የቀረው
- ከዚህ አኳያም ጠቅላላ ጉባኤው ማዕከላዊ ኮሚቴውና ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ በጋራ እንዲያካሂዱት ነው የተወሰነው ይህ አሰራርም በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 15(1) (ቀ) መሰረት የተደገፈ ነው ስለሆነም ሊቀመንበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት ጠቅላላ ጉባኤ ሲጠራ መኪናውን የነበረባቸውን ተግባራትና መከተል የነበረባቸውን ሒደቶች ተከትሎ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራቱንና ለቦርዱ ማረጋገጥ ባለመቻሉና ፓርቲው ከተረጋገጠበት ችግር አንቀጽ በመተዳደሪያ ደንቡ በማያስቀምጠው ሁለተኛው አማራጭን መነሻ በማድረግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴው ጠቅላላ ጉባኤ እንዲጣራ ቦርዱ መወሰኑ የፓርቲው ህጉ ደንብ የተከተለ ስለሆነ የይግባኝ ባይ ክርክር ውድቅ ተደርጎ ቦርዱ የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናልን ሲል መ/ሰጪ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር የሰማ ሲሆን ይግባኝ ባይ በቃል ክርክር ወቅት በመተዳደሪያ ደንቡ መሰረት የሥራ አስፈፃሚ ቁጥር 11 ሲሆኑ የጉባኤ አደራጅ ኮሚቴ ሲዋቀር አንዱ አባል ውጭ አገር ነበር ሁለቱ ከድርጅቱ ተስማምተዋል አራቱ ደግሞ ከድርጅቱ ጋር አብረን አንሰራም በማለታቸው የተነሳ ቀርቷል ስለሆነም የቀሩት አራት አባላት ሲሆን በአዋጁ መሰረት የጉደሉትን የሥራ አስፈፃሚ አባላት በአንድ ወር ውስጥ ማሟላት ማህበሩ ይጠበቅበት ነበር ነገር ግን በኮቪድ -19 ወረርሽኝ በሽታ ምክንያትና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅም ስለነበረ የተገቋደሉትን የሥራ አስፈፃሚ አባላት ሊያሟላ ያልቻለ መሆኑን ገልጸዋል መ/ሰጪ ግን በፅሑፍ የሰጠውን ሀሳብ በሚያጠናክር መልኩ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ተከራካሪዎች ክርክርም በዚሁ መልክ ተጠናቅቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከህግ ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በዚሁም መሰረት በይግባኝ ባይ ማህበር ስራ አስፈጻሚ አባላት መካከል አለመግባባት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም በይግባኝ ባይ ማህበር ስራ አስፈፃሚ አባላት መካከል አልመግባባት ተፈጥሮ ከሆነስ ጠቅላላ ጉባኤው መጥራት ያለበት የማህበሩ ሊቀመንበር ነው ወይስ የማህበሩ

ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ ነው የሚሉትን ነጥቦች ፍ/ቤቱ በጨብጥነት በመያዝ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

በዚሁም መሰረት የመጀመሪው ጭብጥ በተመለከተ

- ይግባኝ ባይ ማህበር ጥር 01 ቀን 2013 ዓ/ም በሊቀመንበሩ አማካኝነት ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቶ የነበረ ሲሆን በተለይ ከስራ አመራር ምርጫ ጋር በተያያዘ ማጭበርበር ተፈፅመዋል በሚል በስራ ላይ ባለው ስራ አስፈፃሚ መካከል አለመግባባት መፈጠሩንና ይህ አለመግባባትም በጊዜው መፍትሔ ባለማግኘቱ ማህበሩ አራት የስራ አስፈፃሚ አባላት ይዞ የቀረ ሲሆን ሰባቱ አባላት ግን ላይ በተገለፀው ምክንያት በስራ አስፈፃሚ አባላት ስብሰባ ለመከፈል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርቷል፡፡

ይግባኝ ባይ ማህበርም እነዚህ የተጓደሉትን የማህበሩ ስራ አስፈፃሚ አባላት ህጉ በሚፈቅደው መሰረት ከማህበሩ ማዕከላይ ኮሚቴ በአንድ ወር ውስጥ ምርጫ በማካሄድ ሟሟላት ሲገባው ይህንኑ ግዴታው ባለመቀጣቱ የተነሳ በማህበሩ ህልውና ላይ አደጋ እንዲያንዣብብ አድርገዋል፡፡

ይግባኝ ባይ ማህበር ለሰኔ 04 ቀን 2014 ዓ/ም በሊቀመንበሩ እንዲካሄድ የጠራው ጠቅላላ ጉባኤም የጉባኤው አደራጅ ኮሚቴ ምልአተ ጉባኤ ሳይኖረው በአራት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ብቻ የተሰየመ ከመሆኑ የተነሳ የጉባኤው አደራጅ ኮሚቴ አወቃቀር የማህበሩን ህገ ደንብ ያላከበረ መሆኑን ያሳያል፡፡

ስለሆነም ወደ ሁለተኛው ጭብጥ ስንመለስ በይግባኝ ባይ ማህበር ስራ አስፈፃሚ አባላት መካከል አለመግባባት መፈጠሩን ተከትሎ ወደ ማህበሩ ማዕከላይ ኮሚቴ እና መላ የማህበሩ አባላት አለመግባባቱ የዘለቀ መሆኑን ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኝ ተከራካሪዎች ክርክር ሊገናዘብ ችለዋል፡፡

ይህ ሁሉ የሚያሳየው በየደረጃው ያሉት አመራሮች የተፈጠረው አለመግባባት በይግባኝ ባይ ማህበር ሕልውና ላይ አደጋ ያንዣበበ መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ባይ ማህበር ካንዣበበት የህልውና አደጋ መወጣት የሚቻለው የማህበሩ ህገ ደንብ አንቀጽ 15.1.2(ቀ) መሰረት የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ መጥራት ያለበት የማህበሩ ሊቀ መንበር ሳይሆን የማህበሩ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አማካኝነት መሆን እንዳለበት ፍ/ቤቱም አቋም ይዞበታል፡፡

ከዚህ አንፃር የመ/ሰጪ መ/ቤት በቁጥር አ1162/11/678 በ13/11/2014 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ሕግን መሰረት ያደረገ ስለሆነ የሚነቀፍበት ምክንያት የለውም ስለሆነም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል።

## ው ሳ ኔ

1) የመ/ሰጪ መ/ቤት በቁጥር አ1162/11/678 በቀን 13/11/2014 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል።
2) ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የየራሳቸው እንዲችሉ ተወስነዋል።

## ት እ ዛ ዝ

1) ይህ ፍ/ቤት በ09/12/2014 ዓ/ም ሰጥቶት የነበረው የዕግድ ትእዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ።
2) ይግባኝ ማለት መብት ነው።
3) መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የዳኞች ፊርማ አለው

ኤ/ቀ

30/12/2014

.